# ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

| | |
|---|---|
| የተዛመዱ ርእሶች፡- | BLC፣ COB-RA፣ ECC-RA፣ JFA፣ JFA-RA፣ JGA፣ JGA-RA፣ JGA-RC፣ JNA-RB |
| ሃላፊ ፅ/ቤቶች፡- | የት/ቤቶች የድጋፍና መሻሻል ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ<br>ዋና የሥራ ሀላፊ<br>የአካዴሚ ዋና ኃላፊ |

## መታገድ እና መሰናበት

### I. ኣላማ

ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ሰራተኞች በማስተማርና በመማር ያተኮረ ስርኣት ያለውና ሰላማዊ አካባቢ ለመንከባከብ ተከባብረው ~~ኣብረው~~ የሚሰሩበት ማህበረሰብ ነው። ተማሪዎች ፅኑ ለሆኑ፣ ተገቢ፣ እና በፍትህ የሚተገበር የግለሰቦችንና የማህበረሰቡን መብቶች የሚያከብር የዲሲፕሊን ሂደት መብት ኣላቸው።

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) መመርያ JGA፣ *የተማሪ ዲሲፕሊን*፣ በMontgomery County Public Schools (MCPS) ያስቀመጠዉ ተፈላጊዎቹን የዲሲፕሊን ሂደት—

A. የማስተማር እና የመማሪያ ድጋፍ ለማድረግ ተከታታይ ትምህርታዊ ስልቶች እና የዲሲፕሊን ግብረመልሶች ያካተቱ፤

B. ኣወንታዊ ስነምግባር መንከባከብ፣ እና፣ በተቻለ ሁኔታ፣ የተማሪን ኣሉታዊ ስነምግባር ከመከሰቱ በፊት መከላከል፤

C. ተማሪዎች ከስህተቶቻቸው ለመማር እድል እንዲኖራቸው የሚያስችል መልሶ ገንቢ የዲሲፕሊን ፍልስፍና ማንፀባረቅ፣ በስነምግባራቸው ምክንያት የተፈጠሩ ማናቸውንም ጉዳት ማረም፣ እና በስነምግባራቸው የተቋረጡ ግንኙነቶችን መልሶ መገንባት፤

D. የተራዘሙ እገዳዎችን ወይም መሰናበቶችን እንደ የመጨረሻ መጠጊያ ኣማራጮች ብቻ መጠቀም፤ እና

E. ተማሪዎች ተመርቀው ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁ እንደሚሆኑ ኣድርጎ በት/ቤት ውስጥ እንዲሳተፉ መያዝ።

### II. ፍቺዎች

*ዋናው የስራ ሃላፊ/chief operating officer* (COO) የእገዳዎችንና የመሰናበቶችን ውሳኔዎች በሚመለከት የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ተወካይ ነው።

B. *ውይይት/Confer* ማለት ውይይት ወይም መነጋገር በማንኛውም ዘዴ፣ ለምሳሌ፣ ቴሌፎን፣ የኤሌክትሮኒክ ሜይል፣ ፊት-ለፊት ግንኙነት፣ የመምህሩ ኣስተያየቶች የሚተላለፉበትና የሚገናዘቡበት ማለት ነው።

C. ኣንድ *ስንብት/expulsion* ማለት የተማሪው/ዋ ከተማሪው/ዋ መደበኛ የት/ቤት ፕሮግራም ለ45 የትምህርት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ መወገድ፣ ወላጅ/አሳዳጊን በማስታወቅ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ለደርስ የሚችል ማለት ነው፡-

1. COOው/ዋ ከስንብት ጊዜ ፍፃሜ ኣስቀድሞ የተማሪው/ዋ መመለስ በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት የሚያስፈራ ስጋት የሚያስከትል ነው ብሎ/ላ ከወሰነ/ች።

2. COOው/ዋ የስንብቱን ጊዜ ተግባራዊ ሊሆን ለሚችልበት ከሁሉም በታች ላነሰ ጊዜ ኣሳጥሮታል/ኣሳጥረዋለች።

3. የት/ቤቱ ስርኣት የተሰናበተ(ች)ውን ተማሪ ወደ መደበኛ ኣካዴሚያዊ ፕሮግራም በስኬታማ ሁኔታ መመለስን ለማራመድ ሚዛናዊ/ ተመጣጣኝ የሆኑ ትምህርታዊ ኣገልግሎቶች እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ ኣገልግሎቶች ያቀርባል።

D. እገዳ

1. *መታገድ (በት/ቤት-ውስጥ)* ማለት በት/ቤቱ ህንፃ ውስጥ የተማሪው/ዋ ከተማሪው/ዋ ወቅታዊ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በኣንድ የትምህርት ኣመት ወስጥ እስከ 10 ቀኖች ነገር ግን ከዚህ ጊዜ ላልበለጡ የትምህርት ቀኖች ወላጅ/ኣሳዳጊን በማስታወቅ በት/ቤቱ ርእሰመምህር መወገድ ማለት ነው።

   ኣንድ በት/ቤት-ውስጥ መወገድ እንደ የኣንድ ቀን መታገድ ኣይታሰብም ተማሪው/ዋ የሚከተሉትን እድሎች ማግኘት እስከቻለ/ች ድረስ—

   a) በኣጠቃላይ ስርኣተትምህርት በሚገባ መገስገስ፤

   b) በተማሪው/ዋ Individualized Education Program/ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተወሰኑ ልዩ ትምህርትንና የተዛመዱ ኣገልግሎቶች መቀበል፣ ተማሪው/ዋ በ*ሜሪላንድ ደንቦች ኮድ* (COMAR) 13A.05.01 መሰረት ስንክልና ያለው/ያላት ተማሪ ከሆነ/ች፤

   c) ለተማሪው/ዋ በመደበኛ የመማርያ ክፍል ሊሰጠው/ጣት የሚችል ፕሮግራም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት መቀበል፤ እና

   d) ኣግባብነት እስካለዉ ድረስ፣ በተማሪው/ዋ ወቅታዊ የመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ተማሪው/ዋ ያ(ታ)ደርግ እንደነበረው ከዕድሜ እኩዮቹ/ቿ ጋር የመሳተፍ።

2. ኣንድ *መታገድ (ለኣጭር-ጊዜ፣ ከት/ቤት-ውጭ)* ማለት የኣንድ ተማሪ በዲሲፕሊን ምክንያቶች ከተማሪው/ዋ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እስከ ሶስት የትምህርት ቀኖች ነገር ግን ከዚያ ለማይበልጥ ጊዜ ለወላጅ/ኣሳዳጊ በማስታወቅ በርእሰመምህር መወገድ ማለት ነው።

3. *መታገድ (ለረጅም-ጊዜ፣ ከት/ቤት-ውጭ)* ማለት የኣንድ ተማሪ ከተማሪው/ዋ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በ4 እና በ10 የትምህርት ቀኖች መካከል ለሆነ ጊዜ በዲሲፕሊን ምክንያቶች ለወላጅ/ኣሳዳጊ በማስታወቅ በርእሰመምህር መወገድ ማለት ነው።

4. *መታገድ (የተራዘመ፣ ከት/ቤት-ውጭ)* ማለት የኣንድ ተማሪ ከተማሪው/ዋ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በ11 እና በ45 የትምህርት ቀኖች መካከል ለሆነ ጊዜ፣ ለወላጅ/ኣሳዳጊ በማስታወቅ መወገድ፣ ይህም በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ሊደርስ የሚችል፡-

   a) COOው/ዋ የሚከተለውን ወስኗል/ኣረጋግጧል/ወስናለች/ኣረጋግጣለች—

(1) ከእግዳው ጊዜ ፍፃሜ አስቀድሞ የተማሪው/ዋ መመለስ በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳትና የሚያስፈራ ስጋት የሚያስከትል ከሆነ፤ ወይም

(2) በሌሎች ተማሪዎች ላይ በትምህርት ሙሉውን ቀን ከባድ መሰናከል በፈጠረ ስር በሰደደና በከፍተኛ የትምህርት ሂደት ረብሻ ተማሪው/ዋ ተሳትፏል/ተሳትፋለች፣ እናም ሌሎች በቅርብ የሚገኙና ተገቢ ስነምግባራዊና ዲሲፕሊናዊ ጣልቃገብነቶች ተሟጥጠዋል።

b) COOው/ዋ የመወገዱን ጊዜ ተገባራዊ ሊሆን ለሚችልበት ከሁሉም በታች ላነሰ ጊዜ ኣሳጥሮታል/ኣሳጥረዋለች።

c) የት/ቤቱ ስርኣት የተወገደ(ች)ውን ተማሪ ወደ መደበኛ ኣካዴሚያዊ ፕሮግራም በስኬታማ ሁኔታ መመለስን ለማራመድ ሚዛናዊ/ተመጣጣኝ የሆኑ ትምህርታዊ ኣገልግሎቶች እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ ኣገልግሎቶች ያቀርባል።

## III. ለተማሪ ዲሲፕሊን መመርያዎች

A. ተማሪዎች ለስርኣት-ኣዘል እና ለሰላማዊ የመማርያ ኣካባቢ፣ እናም ለፅኑ፣ ተገቢ፣ እና በፍትህ ለሚተገበሩ የዲሲፕሊን ተግባራት/ተሞክሮዎች መብት ኣላቸው። የMCPS ሰራተኞች በግልፅ፣ ለእድገት ተገቢ፣ እና በኣስፈላጊ ታሳቢዎች በመጠቀም እና የሚተገበሩ ውጤቶች ሚዛናዊና የፀኑ መሆናቸውን በማረጋገጥ የዲሲፕሊን ውሳኔዎችን ይፈፅማሉ።

B. ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች፣ IEPዎች ወይም ሴክሽን 504 ፕላኖች የዳበሩላቸው፣ በፌደራል ህግ የተወሰኑ መከላከያዎች እሏቸው፣ እናም IEPዎች ወይም ሴክሽን 504 ፕላኖች ላሏቸው ተማሪዎች ዲሲፕሊናዊ ተፈላጊዎች በMCPS ደንብ JGA-RC፣ *ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች መታገድና መሰናበት ላይ ተገልፀዋል።*

C. ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃዎች ኣወሳሰን ላይ፣ ውሳኔ ሰጪዎች ጥሰቱንና የሚከተሉትን ታሳቢዎች ማገናዘብ ኣለባቸው:-

1. የተማሪው/ዋን እድሜ (ከቅድመ-K–3ኛ ክፍል፣ መታገድና መሰናበት በኣጠቃላይ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም። እንዲሁም ክፍል V.ን ከዚህ በታች ተመልከቱ።)

2. ሞየቀድሞ ከባድ ዲሲፕሊናሪ ጥሰቶች (ያለፈው ስነ ስርኣት ጉድለት ጠባይ በማካተት፣ ያለፉት የስነምግባር ጉድለቶች ቁጥር፣ እና ለእንደዚህ ኣይነቱ የስነምግባር ጉድለት የተተገበሩ የዲሲፕሊን እርምጃዎች)

3. የተማሪው(ዋ)ን ስነምግባር ለመገንዘብ ኣውደ ንባብ ሊሰጡ የሚችሉ ቤባህላዊ ወይም የቋንቋ ታሳቢዎች

4. በከውነቱ ዙርያ የሚገኙ ሁኔታዎች

5. ሌሎች የሚያቃልሉ ወይም የሚያባብሱ ሁኔታዎች

D. ካውንቲ-ኣቀፍ የዲሲፕሊን ደረጃዎች

1. ማስተማርንና መማርን የሚደግፉ እና አወንታዊ ስነምግባሮችን የሚንከባከቡ እናም መልሶ የመገንባትን የዲሲፕሊን ፍልስፍና የሚያንፀባርቅ ቀጣይ የማስተማር ስልቶችና የዲሲፕሊን ምላሾች ጥቅም ላይ መዋል ኣለባቸው።

2. የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶች ተገቢ መሆናቸው ሲወሰን፣ የዲሲፕሊን ምላሾች የውሳኔ ሃሳቦች በ*MCPS የተማሪ ስነምግባር ኮድ* ይገኛሉ።

3. መታገድ እና መሰናበት የመጨረሻዎቹ ኣማራጭ ሆነው ይታሰባሉ።

4. የIEPዎች ወይም ሴክሽን 504 የዳበሩላቸው ስንክልና ላላቸው ተማሪዎች፣ ውጤቶቹ በህግ ተፈላጊዎች በMCPS ደንብ JGA-RC፣ *ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች ማገድና ማሰናበት፣ በተገለፀው መሰረት ሊሻሻሉ ይችላሉ።*

E. ስልጣን

1. ርእሰመምህሩ/ሯ/ተወካዩ/ይዋ፣ በት/ቤትውስጥ እገዳ፣ የኣጭር-ጊዜ እገዳ ወይም የረጅም-ጊዜ እገዳ የመተግበር ስልጣን ኣለው/ኣላት።

   ርእሰመምህሩ/ሯ በተጨማሪ የተራዘመ የእገዳ ወይም የስንብት ውሳኔ ሃሳብ፣ በፅሁፍ፣ ለCOOው/ዋ መስጠት ይችላል/ትችላለች።

2. COOው/ዋ የተራዘመ እገዳ መተግበር ወይም ኣንድን ታማሪ የማሰናበት ስልጣን ኣለው/ኣላት።

3. MCPS ኣንድን ተማሪ በዲሲፕሊን ምክንያቶች ወደ ሌላ ት/ቤት ወይም ኣማራጭ የትምህርት ፕሮግራም የማዛወር ስልጣን ኣለው ሙብቱንም የተጠበቀ ነው። ኣንድ ተማሪ በዲሲፕሊን ምክንያቶች ወደ ኣማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ከተላከ፣ በMCPS ደንብ JGA-RC *ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች እገዳ ወይም ስንብት* በሌላ ካልተገለፀ በስተቀር እንደ ጊዜው ኣረዛዘም "የተራዘመ እገዳ ወይም ስንብት" ተብሎ ይታሰባል።

## IV. ቅደም-ተከተሎች ለትምህርት ቤቶች

A. ርእሰመምህሩ/ሯ/ተወካዩ/ይዋ ለዲሲፕሊን ጥሰት ለማንኛውም ወቅት ማገድ ወይም ስንብት ምላሽ ሲሰጥ/ስትሰጥ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ/ተወካዩ/ይዋ የሚከተሉትን ያከናውናል/ታከናውናለች—

1. ማንኛውንም እገዳ ከማስገደድ በፊት ከተማሪው/ዋ ጋር መገናኘት፣ ወይም በተቻለ ፍጥነት ተማሪው(ዋ)ን ከት/ቤት ማግለል ካስፈለግ ምክንያቱም ተማሪው(ዋ) ለግለሰቦች ወይም ለንብረት ኣጣዳፊ ኣደጋ ስለሚ(ምት)ሆን፣ ወይም የትምህርት ሂደቱ ላይ በቀጣይ የረብሻ ስጋት ስለሆነ/ች፣ እናም—

   a) በተማሪው/ዋ ላይ ስለቀረቡ ክሶች ለተማሪው/ዋ ማስታወቅ እና የማስረጃውን ማብራርያዎች መስጠት፣ እናም

   b) ተማሪው(ዋ) ስለክውነቱ ያለው(ላት)ን ሐተታ/ኣስተያየት/version እንዲያ(ድታ)ቀርብ እድል መስጠት፤

2. ለማገድ ወይም ላለማገድ ውሳኔ መስጠት፤ እና

3. ውሳኔው ላለማገድ ከሆነ ተማሪው(ዋ)ን ለአስተላለፈው/ችው የመምህር ማመማሪያ ክፍል ከመመለስ በፊት ከመምህሩ/ሯ ጋር መወያየት።

B. ውሳኔው ተማሪው(ዋ)ን የማሰወገድ ውሳኔ ከሆነ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ/ተወካዩ/ይዋ የሚከተለውን ያከናውናል/ታከናውናለች—

1. ወላጅ/ጇ/አሳዳጊው(ዋ)ን ስለ ማገጃው ከተቻለ ተማሪው(ዋ)ን ከት/ቤት ሰፈር/ግቢ ከማስወገድ በፊት ለማስታወቅ የተቻለዉን ሁሉ ጥረት ማድረግ፣ ልተማሪው/ዋ የእድገት ደረጃ ገንዛቤ እየተሰጠው። 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ያለው/ያላት ተማሪን ጉዳይ በሚመለከት፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የሚኖር፣ ልክ እንደ ትአነስተኛ ተማሪዎች ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ግንኙነቶች መደረግ አለባቸው። ማስታወቂያ በቃል ሊደረግ ይችላል ነገር ግን ለወላጅ/አሳዳጊ የፅሁፍ መገናኛ እንዲከተለው ያስፈልጋል፡ ማስታወቂያው/ማመልከቻው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

   a) ማገጃው ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን እና የጊዜ ብዛት

   b) ክስተቱን ለመገምገም እና በተከታይ እገዳ ላይ ከወላጅ/ከአሳዳጊ ጋር ለመወያየት በተቻለ ፍጥነት ስብሰባ ለማቀድ የስብሰባ ግብዣ ማቅረብ

   c) ወላጅ/አሳዳጊን ስለ ይግባኝ መብት የምክር አረፍተሃሳብ እንደሚከተለው መስጠት፡-

      (1) የአጭርና የረጅም ጊዜ ማገጃዎች መጀመርያ ይግባኝ የሚባሉት ለርእሰመምህሩ/ሯ ነው። የሚቀጠጥለው የይግባኝ ደረጃ የDivision of Pupil Personnel and Attendance Services/የፒውፐል ፐርሶኔል እና የክትትል ኣገልግሎቶች ክፍል (DPPAS) ዳይሬክተር ነው።

      (2) ለተራዘሙ ማገጃዎች ወይም ስንብቶች ይግባኞች በቀጥታ ለCOOው/ዋ እንዲደረግ ይመከራሉ።

   d) ተማሪው/ዋ በወላጅ/አሳዳጊ ካልታጀበ/ች ወይም በማገጃ ሁኔትታዎች በግልፅ በአንፃሩ ካልተፈቀደ በስተቀር ተማሪው/ዋ ወደ ት/ቤት ግቢ መመለስ ኣይ(ት)ችልም የሚል ወላጁ/ጇ/ኣሳዳጊው/ዋን የሚመክር ኣረፍተሃሳብ።

2. የMCPS ፎርም 560-6፣ *የቀመር ሉህ/Worksheet ለማገጃ ወይም ከጤና-ጋር-ለተያያዘ መወገጃ መሙላት፣* እና መረጃዎችን ከቀመር ሉህ ወደ OASIS ማሸጋገር። የፎርም 560-6 ቅጂ በተማሪው አጠቃላይ ፋይል መያዝ።

3. የታገደ(ች)ውን ተማሪ ተማሪው/ዋ በት/ቤት-ስፖንሰር በሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዳይ(ድት)ሳተፍ ምክር መስጠት።

4. ተማሪው/ዋ ወደ መማሪያ ክፍል ከመመለሱ/ሷ በፊት ተማሪው/ዋን ከአስተላለፈ(ችዉ) መምህር ጋር መወያየት።

5. አነስተኛ የትምህርት ኣገግሎቶች መሰጠቱን እንደሚከተለው ማረጋገጥ፡-

ተጠያቂነትን ለመመስረት እና የታገዱ ወይም የተሰናበቱ ተማሪዎችን የትምህርት ክፍል ስራን እንዲከታተሉ ለማስቻል፣ እያንዳንዱ ት/ቤት ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉትን የትምህርት አገልግሎቶችን ያቋቁማል፡-

a) እያንዳንዱ/ዷ በተለዋጭ የትምህርት ፕሮግራም ያልተመደበ/ች ከትቤት-ውጭ የታገደ/ች ወይም የተሰናበት/ች ተማሪ በየሳምንቱ በመምህራን የሚገመገምና ታርሞ ለተማሪው/ዋ የሚመለስ የትምህርት ክፍልና የቤት ስራዎች በየእለቱ ከእያንድንዱ መምህር ይቀበላል/ትቀበላለች።

b) በመምህራንና ከት/ቤት-ውጭ በእገዳ ወይም በስንብት በሚገኙ የተለያዩ ተማሪዎች መካከል የሚያገናኝ እና ከነዚያ ከት/ቤት-ውጭ ከታገዱት/ከተሰናበቱት ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አስሳዳጊዎቻቸው ጋር ስለመማርያ ክፍል ስራዎችና ከት/ቤት ጋር ግንኙነት ስላላቸው ጉዳዮች በየሳምንቱ በቴሌፎን ወይም በኢሜይል የሚገናኝ የት/ቤት ሰራተኛ አገናኝ መኮንን እንዲ(**ድት**)ሆን እያንዳንዱ/**ዷ** ርእሰ-መምህር ይሰይማል/**ትሰይማለች**።

c) ለአጭር-ጊዜ እገዳዎች፣ ት/ቤቶች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡-

(1) የአጭር-ጊዜ ማገጃ የሚቀበሉ ሁሉንም ተማሪዎች በማገጃ ወቅት የሚስቱትን/የሚያመልጣቸ**ውን** አካዴሚያዊ ስራ ያለ ቅጣት እንዲፈፅሙ እድል መስጠት፤ እና

(2) የአጭር-ጊዜ ማገጃ ለሚቀበሉ ለሁሉም ተማሪዎችን፣ እና ለወላጆች/አሳዳጊዎቻቸው፣ በክፍል IV.B.5.a) የተገለፀው ተፈላጊ መሟላቱን ለማረጋገጥ ሃላፊ የሚሆነውን የት/ቤት ተቀጣሪ ጋር መገናኛ መረጃ መስጠት።

(3) የተሳቱ ስራዎች በመቀበል ላይ የሚገኙ የታገዱ ተማሪዎች ሁሉም የሂደቱ ሌሎች ገፅታዎች፣ የተሳቱ ስራዎችን መፈፀም፣ እና ፈተናዎችን ማከናወን ከእያንዳንዱ በፈቃድ በመቅረት ከሚከናወን የማስተካከያ ስራ ከተመሰረተዉ መመርያና ልምድ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

6. ተገቢ ከሆነ፣ የዲሲፕሊን ጥሰት እንዳይደገም ለመከላከል የተተለመ ፕሮግራም ለማዳበር ከተማሪው/ዋ እና ወላጅ/አሳዳጊ ጋር አብሮ መስራት።

## V. በቅድመ-K – 2ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች የዲሲፕሊን ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. የቅድመ-K – 2ኛ ክፍል ተማሪን ስነምግባር ለመቆጣጠር ት/ቤቶች ጣልቃገብነትና ድጋፍ መስጠት አለባቸው ተማሪው/ዋ ከታገደ/ች፤ ለት/ቤት አካባቢ ረባሽ ከሆነ/ች፤ ወይም የተማሪው/ዋ የክፍል ደረጃ ባይ(ት)ሆን ኖሮ ለማገጃ ያደርሳል ተብሎ የሚገመት ተግባር ከፈፀመ/ች።

1. ጣልቃገብነትና ድጋፍ ከ**ሚ**ከተሉት ማናቸውንም ያካትታል-

a) አወንታዊ የስነምግባር ጣልቃገብነቶችና ድጋፎች፤

b) የተሻለ የጣልቃገብነት ፕላን፤

c) ለተማሪ ድጋፍ ቡድን ማስተላለፍ/መላክ፤

d) ለIEP ከፍጪሴክሽን 504 ፕላን ማስተላለፍ/መላክ፤ ወይም፣

e) ትኣግባብ ለሆኑ ማህበረሰብን መሰረት ላደረጉ አገልግሎቶች ማስተላለፍ።

2. ት/ቤቱ በተገቢ የጣልቃገብ ዘዴዎች፣ በMCPS *የተማሪ ስነምግባር ኮድ* በተገለፀው መሰረት የማገገሚያ ድርጊቶችን ጨምሮ፣ የተማሪው(ዋ)ን ስነምግባር ጉዳት መፈወስ ኣለበት።

B. የቅድመ-K – 2ኛ ክፍል ተማሪ ስነምግባር በMCPS *የተማሪ ስነምግባር ኮድ* መሰረት መታገድ ከጠየቀ፣ የሚከተለው ተግባራዊ ይሆናል፦

1. ርእሰመምህሩ/ሯ/ተወካዩ/ይዋ ከት/ቤት ሳይኮሎጂስት ወይም የሳይኮሎጂ ኣገልግሎቶች ኣስተባባሪ/ዳይረክተር ጋር በሌሎች ጣልቃገብነቶችና ድጋፎች ሊወገድ የማይችል በሌሎች ተማሪዎችና ሰራተኞች ላይ የከባድ ጉዳት ስጋት በማንዣበብ ላይ እንዳለ ለመወሰን መወያየት ኣለበ(ባ)ት።

2. የት/ቤቱ ርእሰመምህር/ተወካይ በማገጃ መቀጠል ከወሰነ/ች፣ ርእሰመምህሩ/ሯ/ተወካዩ/ይዋ በት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ፅ/ቤት ተገቢውን ዳይረክተር እንዲያ(ድታ)ፀድቅ መገናኘት ኣለበ(ባ)ት።

3. መታገድ ከፀደቀ፣ የማገጃ ርዝመት ከኣምስት የትምህርት ቀኖች መብለጥ የለበትም።

C. በቅድመ-K-2ኛ ክፍሎች የሚ(ምት)ገኝን ተማሪ የማሰናበት የውሳኔ ሃሳቦች በፌደራል ህግ ተፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች (ማለት፣ የጦር መሳርያን የሚያካትት ሲሆን) ብቻ የተወሰኑ ናቸው።

## VI. ማገጃዎችን/ስንብቶችን የመገምገም ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. በወላጅ/ኣሳዳጊ ጥያቄ፣ እናም ከርእሰመምህር ዳግመ-ግንዛቤ በኋላ፣ የDPPAS ዳይሬክተር የኣጨር- ወይም የረጅም-ጊዜ ማገጃ ለመስጠት ውሳኔዎችን ሊ(ልት)ገመግም ይችላል/ትችላለች።

B. የኣጨር- ወይም የረጅም-ጊዜ ማገጃ ለመስጠት የርእሰመምህሩ(ሯ)ን ውሳኔዎች ለመገምገም፣ የDPPAS ዳይሬክተር የሚከተሉትን ያከናውናል/ታከናውናለች—

1. ሁሉንም ቁሳቁሶች ከርእሰመምህሩ/ሯ፣ የDPPAS ሰራተኞች፣ ከወላጅ/ኣሳዳጊ፣ ወይም ሌሎች ከውነቱን የሚመለከቱ፣ እና የታሰበሙው/የተደገፈሙውን የድስፐሊን እርምጃ ይገመግማል/ትገመግማለች፤

2. በቴሌፎን መገናኘት ወይም፣ በDPPAS ዳይሬክተር ምርጫ፣ ከርእሰመምህሩ/ሯ እና/ወይም ከወላጅ/ኣሳዳጊ ጋር ስብሰባ መቅጠር፤ እና

3. የፅሁፍ ውሳኔ መስጠት፣ ምክንያቶችን ጨምሮ፣ እና ወላጅ/ኣሳዳጊ በተጨማሪ ለCOO ይግባኝ የማለት መብት እንዳላቸዉ ለወላጅ/ኣሳዳጊ ማስታወቅ።

C. ኣንድ ርእሰመምህር የተራዘመ ማገጃ ወይም ስንብት የውሳኔ ሃሳብ ካቀረበ/ች፣ ርእሰመምህሩ/ሯ የውሳኔ ሃሳቡን እድያውኑ ለCOO ፅ/ቤት ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

ለተራዘመ ማገጃ ወይም ስንብት የውሳኔ ሃሳብ ከአንድ ርእሰ-መመምህር እንደተቀበሉ በCOO ፅ/ቤት የሚገኙ ሰራተኞች ከDPPAS ሰራተኞች እና ከት/ቤቱ ጋር አብረው ይሰሩ እና ስለቀረበው ትግባሬ ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ፣ እንዲሁም ለወላጅ/አሳዳጊ ስለ ቀን፣ ሰአት፣ እና የስብሰባ ቦታ በCOO የተሰየመ የችሎት መኮንን፣ ተማሪ/ዋ፣ የተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና የት/ቤት ሰራተኛ ያሳውቁ(ቋ)ታል፤ እና

2. ከስብሰባው በኋላ፣ COOው/ዋ የተራዘመ ማገጃ ወይም ስንብት አስፈላጊ እንደሆን ይወስናል/ትወስናለች፣ አንድ ቅጂ ለተማሪው/ዋ ወይም ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ ይልካል/ትልካለች ፣ እናም ውሳኔ ከተሰጠበት በ10 የቀን መቁጠርያ ቀኖች ውስጥ ለቦርዱ የይግባኝ መብት ማስታወቂያ ያካትታል/ታካትታለች። የቦርዱ የይግባኝ ቅደም-ተከተል በቦርድ መምርያ BLB፣ *የይግባኞችና የችሎቶች ሂደቶች ህጎች* ውስጥ ተሰጥቷል።

D. ከት/ቤት የታገደ/ች ወይም የተሰናበተ/ች ተማሪ የማገጃ ወይም የስንብቱ ሁኔታዎች በተሟሉበት ቀን ወደ ት/ቤት እንዲ(ድት)መለስ መቻል አለበ(ባ)ት፣ በተማሪው/ዋ ወይም በወላጅ/አሳዳጊ ለማገጃዉው የይግባኝ ፋይል ቢከፈትም ባይከፈትምም፣ ማገጃውን ወይም ስንብቱን ለተወሰነ ጊኤ ለማራዘም COOው/ዋ ካልወሰነ/ች ምክንያቱም የተማሪው/ዋ ከተወሰነው ተጨማሪ ጊዜ ከማለቁ በፊት ወደ ት/ቤት መመለስ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች የከባድ ጉዳት ስጋት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር።

E. በዚህ ደንብ ክፍል V የተገለፀው ሂደት በመጀመርያው ማገጃ በአስረኛው የትምህርት ቀን ይፈፀማል። ሂደቱን ለመጨረስ ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ስላልነበሩ በደረሱት መዘግየቶች ወይም በምርመራው ውስብስነት የተነሳ፣ ተማሪው/ዋ ወደ ት/ቤት እንዲ(ድት)መለስ የፈቀድለ(ላ)ታል፣ COOው/ዋ የተማሪው/ዋ ወደ ት/ቤት መመለስ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች የከባድ ጉዳት ስጋት ያስከትላል ብሎ/ላ ካልወሰነ/ች በስተቀር።

F. ተማሪው/ዋ ከአስረኛው ቀን በኋላ ወደ ት/ቤት መመላስ ካልቻለ/ች፣ COOው/ዋ በ24 ሰኣት ውስጥ ተማሪዉው(ዋ)ን እና ወላጅ/አሳዳጊው(ዋ)ን ያ(ታ)ስታውቅ እና ስለሂደቱ መዘግየትና፣ የመልሶ መግባት መከልከል ምክንያቶች ይሰጣል/ትሰጣለች እናም የማስታወቂያውን ቅጂ ለሜሪላንድ ስቴት የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ይልካል/ትልካለች።

## VII. የመመለስ ሂደቶች

ርእሰመምህሩ/ሯ ተማሪ የስቴትና የአካባቢ ህግ ወይም ደንብ በሚ(ምት)ጥሰበት ወቅት ወይም በሱ ምክንያት በንብረት ዋጋ ለሚደርሰው ጉዳት ወይም የዋጋ መቀነስ በMCPS ደንብ ECC-RA፣ *ለMontgomery County Public Schools ንብረት መጥፋት ወይም መጎዳት፣* እና የMCPS ደንብ JNA-RB፣ *የተማሪ ፋይናንሳዊ ግዴታዎች አሰባሰብ፣* ሂደቶችን ይከተላል/ትከተላለች።

አንድ/ዲት ተማሪ የስቴት ወይም የአካባቢ ህግ በመጣስ በት/ቤት ነብረት የሚበላሽበት ወቅት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ተማሪው/ዋን ወይም ወላጅ/አሳዳጊን እስከ $2,500 ድረስ እንዲከፍሉ ይጠይቃል/ትጠይቃለች፣ ተማሪው/ዋ ወደ ሜሪላንድ የወጣቶች አገልግሎቶች መምርያ/Department of Juvenile Services *ካልተላለፈ/ች በስተቀር።*

## VIII. የማገጃዎችና የስንብቶች መዛግብቶች መንክብካብ እና ማጥፋት

A. ርእሰመምህሩ/ሯ፣ የDPPAS ዳይሬክተር፣ ወይም COO አንድ ማገጃ ወይም ስንብት መከናወን ኣልነበረበትም ብለው ከወሰኑ፣ የዲሲፕሊን ሂደቶቹን የሚመለከት ሁሉም መረጃዎች፣ የMCPS ፎርም

560-6፣ *የቀመር ሉህ/Worksheet ለማገኛ ወይም ከጤና-ጋር-ለተያያዘ ስንብትን* ጨምሮ፣ ከተማሪው መዝገብ ባፋጣኝ ይወገዳል፣ እናም ይህንኑ የሚመለከት በግለሰብ የሚለይ መረጃ ለማንም ሰው አይተላለፍም።

B. የማገኛን ወይም የስንብትን ዘገባዎች ከተማሪው/ዋ ኤሌክትሮኒክ መዛግብት ለመሰረዝ፣ የተማሪው/ዋ ማገኛ ፎርም፣ MCPS ፎርም 560-6፣ *የቀመር ሉህ/Worksheet ለማገኛ ወይም ከጤና-ጋር-ለተያያዘ ስንብት*፣ ዋናው ቅጂ፣ በርእሰመምህሩ/ሯ የተፈረመበት ማስታወሻ ጋር፣ መዝገቡ እንዲሰረዝ ለሙዋናው/ዋ የቴክኖሎጂ ሃላፊ መላክ አለበት። የመሰረዣ ማረጋገጫ ልውውውጦች/transactions ት/ቤቱ ከተቀበለ በኋላ ዋናው ቅጂ እንዲጠፋ ይደረጋል።

C. የተረጋገጡ የማገኛ ወይም የስንብት ክውነቶችን በሚመለከት ሁሉም መዛግብቶችና ሰነዶች በርእሰመምህሩ/ሯ በMCPS ደንብ JOA-RA *የተማሪ መዛግብት መሰረት በእንክብካቤ ይያዛሉ።*

D. MCPS ስለ ማገኛዎችና ስንብቶች የተጠቃለሉ መረጃዎች ሊንከባከብ ይችላል፣ በግለሰብ ደረጃ ሊለዩ የሚችሉ መረጃዎችን ሳያጋልጥ፣ ህጋዊና እውቅና ላላቸው ለትምህርታዊ ተግባሮች አገልግሎት እንዲውሉ።

**የተዛመዱ ምንጮች፡-** የሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጾች §7-305፣ §7-305.1፤ *የሜሪላንድ ድንቦች ኮድ/Code of Maryland Regulations* (COMAR) 13A.08.01.11፤ 13A.05.01

***የደንብ ታሪክ፡-*** አስቀድሞ ደንብ ቁ. 515-3፣ ፌብሩወሪ 21፣ 1979፤ የማውጫ መረጃ የታደሰው 1983፤ ዲሰምበር 1986 ተከለሰ፤ ጁላይ 26፣ 1989 ተከለሰ፤ ጁን 17፣ 1994 ተከለሰ፤ ጁላዩ 30፣ 1997 ተከለሰ፤ ጁላይ 22፣ 1998 ተከለሰ፤ ፌብሩወሪ 28፣ 2006 ተከለሰ፤ ጁላይ 21፣ 2014 ተከለሰ፤ ሴፕተምበር 27፣ 2017 ተከለሰ።.